የፈሰሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ ዕቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ወይም ጉዳት ሲያገኛቸዉ ወይም የማስረከቢያ ጊዜው ቢዘገይ በኃላፊነት የሚጠቅ ሲሆን ከዚህ ኃላፊነት የሚነው ዕቃው የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰው ወይም የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በተቀባዩ ጥፋት ሲሆን ነው፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል የሚባለው ባለእዳው /አጓዡ/ በቅድሚያ በምንም መልኩ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይቻል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡
3. ወደ መኪና ሮጦ የገባን ሰው ለማዳን በተወሰደ ርምጃ ምክንያት በመጓጓዝ ላይ የነበረ ዕቃ ላይ የደረሰ ጉዳት ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ተከስቷል የሚባል አይደለም፡፡



የመ/ቁ. 14605

ቀን ሐምሌ 29/1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት

ተጠሪዎች፡- 1. ኮሜት ትራንስዓርት ድርጅት
2. ሸበሌ ትራንስፖርት ድርጅት
3. በከልቻ ትራንስፖርት ድርጅት
4. ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት
5. አዲስ ሜካኒካል ድርጅት
6. አቶ ዮሐንስ ተሰፋ

## ፍርድ

ለአሁን አቤቱታ መነሻ የሆነው ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጳጉሜ 3/1992 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በዚያ ፍ/ቤት ከ1ኛ-5ኛ ድረስ ባሉት ተጠሪዎች መኪና አቅራቢነት አመልካች 34993 ሊትር ነጭ ጋዝ ናፍታ አስጭኖ ከአሰብ ወደ ባህርዳር በሚጓጓዝበት ወቅት መኪናው በመገልበጡ የተጫነው ነዳጅ በሙሉ ስለፈሰሰ የፈሰሰውን ነዳጅ ዋጋ ብር 51089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ስምንት ሳንቲም/ ከነወለዱ አምስቱም ተጠሪዎች እንዲከፍሉ፡፡ 6ኛውም ተጠሪ የመኪናው ባለንብረት ስለሆነ በአንድነት እና በነጠላ በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አቀራክሮ ነዳጁ የፈሰሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሃይል ሰለሆነ ተጠሪዎቹ በሙሉ ለክሱ ሃላፊ አይደሉም በማለተ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የስር ፍርድ ቤቱን ውሳፀነ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ላይ ሲሆን የአመልካተ ቅሬታ በአጭሩ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች #ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታን; ሲተረጉሙ የህግ ስህተት ፈጽመዋል የሚል ነው ተጠሪዎችም ለቀረበው አቤቱታ መልስ አቅርበዋል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በአንድነት በ17/10/96 በተጻፈ መልስ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ በክሱ ይተካልን፣ ይህ ቢታለፍ ነዳጁ የፈሰሰው ከተባለም የቀድሞ የኢትዮጰያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ከአመልካች ጋር የማጓጓዣ ውል ስላልፈጸመ ለጥፋቱ ሃላፊ አንሆንም፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ሃላፊነት እንደሌለበት በመ/ቁ/9678 እና በመ/ቁ 6979 በሰበር ችሎት ውሳኔ ተሰጥቷል የሚል ነው፡፡

6ኛ ተጠሪ በበኩሉ በ9/6/97 በተጻፈ መልስ ነደጁ የፈሰሰው ከፈቅም በላይ በሆነ መክንያት ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናለት ጥቅቋል፡፡

አመልካችም በመልስ መልሱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ከፍ ሲል የተገለጸው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገው አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም፣

1. አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይስ አይደለም?
2. ካልሆነ ተጠሪዎች ለክሱ ሃላፊ ሊሆኑ ይገባልን? የሚሉት ነጥቦች መታየት አለባቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>

አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በሃላፊነት እንደሚጠየቅ የግን ህጉ ቁጥር 590 ሲያመለክት አጓዡ ከዚህ ሀላፊነት የሚድነው ደግሞ የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰው ወይም የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በእቃው ውሳጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ የን/ህ/ቁ 591 ያመለከታል፡፡

በመሆኑም አንድ አጓዥ የሚያጓጉዘው እቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት ከሆነ ከሃላፊነት ለመዳን እቃው የጠፋው ወይም የተጎዳው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን ወይም ከራሱ ከእቃው ጉድለት መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ሲሆን



ከምክንያቶቹ ውስጥም ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ የሚለው በመሆኑ ችሎቱም ይህ ሁኔታ ተከስቷል የሚባለው መቼ ነው የሚባለውን ከህጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በንግድ ህጉ ውስጥ "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ወደ ፍ/ብ/ህጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ወደሚመለከቱት ድንጋጌዎች ማምራቱ የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረትም የፍ/ህ/ቁ 1792ን ስንመለከት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ወይም የለም የሚባለው መቼ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ሀይል ደርሷል የሚባለው ባለእዳ ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍጹም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ከንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለእዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈጻጸም ከባድ የሆነ ወጪ በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት መመልከት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለእዳው በቅድሚያ በምንም መልኩ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለእዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብ እና ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት ማየት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል የሚችለው ፈጽሞውኑ ሊቋቋሙት ወይም ሊቆጣጠሩት የማይቻል ወይም ማንኛውም ጠንቃቃ ሰው ሊገምተው እና ሊያስበው የማይቻለው ሁኔታ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1793 የተዘረዘሩት ምክንያቶችም ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይም ስናመራ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ነጻ ያደረጓቸው ነዳጁ የፈሰሰው ወደ መኪናው ሮጦ የገባን ሰው ለማዳን በተወሰደ እርምጃ ስለሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ድንገተኛ ደራሽ አደጋ ነው በማለት ነው፡፡ ነገር ግን አንድ

የመኪና አሽከርካሪ መኪያ በሚያሽከረክርበት ወቅት በመንገዱ ድንገት ሰው ሊገባበት እንደሚችል፣ የተለያዩ የመጋጨት ወይም የመገልበጥ አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል ቀደም ብሎ ሊገምት ወይም ሊያስብ የሚችለው ነገር ነው፡፡ የመኪና አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ጊዜ በመንገዱ ላይ ድንገት ሰው ሊገባ ወይም ድንገተኛ አደጋ ሊያጋጥም ይችላል ብሎ ፈጽሞ አያስብም ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም 6ኛ ተጠሪ መኪናውን ሲያሽከረክር ድንገት ሰው ሮጦ ወደ መንገዱ መግባቱ ብቻ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ መኖሩን አያሳይም፡፡ ስለዚህም የስር ፍ/ቤቶች ለነዳጁ መፍሰስ ምክንያት የሆነውን አደጋ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለጸው አንድ አንኙ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡ ከኃላፊነቱ ነጻ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንደኛው ደግሞ አደጋው ወይም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 6ኛ ተጠሪ አንኙ መሆኑ ክርክር አልተነሳበትም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ደግሞ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንየት አይደለም፡፡ ስለዚህም 6ኛ ተጠሪ ለጉዳቱ በን/ህ/ቁ 590 መሠረት ኃላፊ ነው፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉትን ተጠሪዎችን ኃላፊነት ስንመለከት ተጠሪዎቹ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው የማይባል ከሆነ የፈረሰው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን እቃውን ለማጓጓዝ ከአመልካች ጋር ያደረገው ውል ስለሌለ ኃላፊነት የለብንም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን አንጂ በስር ፍ/ቤት የፈረሰው ድርጅት የእቃ ላኪ ኮሚሲዮን እቃ አንገዥ ያለበት መብት እና ግዴታ ያለበት በመሆኑ (የፍ/ህ/ቁ. 2252 (3)) ተጠሪዎቹ ለደረሰው ጉዳት በአንድነት አና በነጠላ ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በተጨማሪ ያነሱት ክርክር በተመሳሳይ ጉዳት ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ኃላፊነት እንደሌለበት ቀደም ሲል ተወስኗል የሚል ሲሆን እንደዚህ አይነት ውሳኔ ተሰጥቶ እንኳን ቢሆን በተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ይሆንም፡፡

በመጨረሻም እነዚሁ ተጠሪዎች ወደ አክስዮንነት የተቀየርን ስለሆነ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ተተክቶ ይከራከር ሲሉ የጠየቁ ቢሆንም ቦርዱ በኃላፊነታቸው መጠን እዳቸውን የመክፈል ግዴታ ካለበት በአፈጻጸም ጊዜ እንዲተካ ሊጠይቁ የሚችሉ በመሆኑ ጥያቄያቸው በዚሁ ታልፏል፡፡



## <u>ውሣኔ</u>

- ተጠሪዎች በአንድነት እና በነጠላ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈሉ፡፡
- አመልካች በክርክሩ ወቅት ለደረሰበት ወጪ እና ኪሣራ ዝርዝሩን በስር ፍ/ቤት አቅርቦ ያስወስን፡፡
- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 349/87 በ3/13/92 ዓ.ም. እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2317/93 በ14/3/96 ዓ.ም. የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡